*AMHARIC*

# SEATTLE PUBLIC SCHOOLS—NOTIFICATION OF RIGHTS UNDER THE PROTECTION OF PUPIL RIGHTS AMENDMENT (PPRA)

## የሲያትል ትምህርት ቤቶች የተማሪዎችን መብት አስመልክቶ በወጣው የማሻሻያ ህግ መሰረት ስላለቸው መብት ማሳወቅ፤

የተማሪዎችን መብት በሚጠብቀው የማሻሻያ ህግ መሰረት የሲያትል ትምህርት ቤቶች አስተዳደር በሚያደጋቸው ጥናቶች፣ ለገቢያ አገልግሎት ለማዋል የሚሰበስባቸውና የሚጠቀምባቸው መረጃዎችንና እንዲሁም አንዳንድ ኣካላዊ ምርመራችዎችን በሚመለከት ወላጆችና ከ 18 አመት እድሜ በላይ ያላቸው(ብቁ የሆነ ተማሪዎች) አንዳንድ መብቶች አላቸው። እነዚህም መብቶች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ ፤

• ተማሪዎች ለአንድ ወይም ከዚያ በላይ ቀጥሎ በተዘረዘሩት ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው መረጃዎች( ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው የመረጃ የጥናት መጠይቆች) በሙላት ሆነ በከፊል በዩናይትድ ስቴትስ የትምህርት ሚኒስቴር በኩል የሚከፈል ከሆነ ለጥናት የሚሆን ቃለ መጠይቅ እንዲካፈሉ ከመደረጋቸው በፊት የስምምነት ፈቃድ መኖር አለበት። *እነዚህም፤*

1. የተማሪው ወይም የተማሪው ወላጅ የፖለቲካ ጥገኝነት ወይም እምነት ፤
2. የተማሪው ወይም የተማሪው ቤተሰብ የአእምሮ ወይም የስነኣእምሮ ችግሮች፤
3. የጾታ ባህርይ ወይም ጸባይ ፤
4. ህገ-ወጥ የሆነ፣ ጸረ-ማህበራዊ የሆነ፣ ጥፋትን መታመን ወይም የማቃለል ጸባይ፤
5. ከተጠያቂዎቹ ጋር የቅርብ የቤተሰብ ግንኙነት ያላቸውን የሚነቅፍ ግምገማ፤
6. በህግ እውቅና ካላቸው መብታዊ ግንኙነቶች ለምሳሌ ከህግ አማካሪ፣ዶክተሮች ወይም መንፈሳዊ መሪዎች፤
7. የተማሪው ወይም የወላጅ የሃይማኖት ልምዶች፣ አባልነት ወይም እምነት ፤
8. ለፕሮግራሞች ብቁ መሆናቸውን ለመገምገም ህጉ ከሚያዘው በስተቀር የገቢያቸው መጠን፤

•ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን በሚመለከት ተማሪው አስቀድሞ/ማ ማስታወቂያ እንዲያገኝ/ታገኝ ወይም ላለመካፈል ያለውን እድል እንዲያውቅ/ድታውቅ ማድረግ ፤

1. ማንኛውም ሌላ ሚስጢራዊነቱ የተጠበቀ የመረጃ መጠይቅ፣ ገንዘቡ በማን እንደሚከፈል በማያጠያይቅ ሁኔታ፤
2. ማንኛውም አጣዳፊ ያልሆነ፣አግባብ የሌለው የአካል ምርመራ ወይም የመሳተፍን ሁኔታ ለማወቅ በትምህርት ቤቱ ወይም እርሱን በሚወክሉና የተማሪውን ጤንነትና ደህንነት ለመጠበቅ የሚደረጉ ማጣሪያዎች ካልሆኑ በስተቀር፣ ይህም የመስማትን፣ የማየትን ወይም የወገብ አጥንት ምርመራ ወይም ማንኛውም የአካል ምርመራ ወይም ማጣሪያ በመንግስት ህግ ካልተፈቀደና አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ፤
3. ለገቢያ ለማስተዋወቅ ወይም ለመሸጥ ወይም መረጃን ለሌሎች ለማሰራጨት ከተማሪዎች የግል መረጃን ለመሰብሰብ፣ ግልጽ ለማድረግ ወይም ለመጠቀም የሚደረግ እንቅስቃሴዎች፤

•በሚጠየቅበት ወቅት ወይም ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት መቆጣጠር፤

<u>*AMHARIC*</u>

1. የተጠበቁ የተማሪዎች የመረጃ መጠይቆች፤
2. ከላይ ከተጠቀሱስ ለገበያ ለማስተዋወቅ፣ለመሸጥ ወይም ሌላ ለማሰራጨት አላማ ሲባል ከተማሪዎች የግል መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚጠቀሙባቸው መሳሪያዎች ፤
3. የትምህርት ስነ-ስርአት(ካሪኩለም) ክፍል የሆነ የትምህርት ቁሳቁስ ፤

የሲያትል ትምህርት ቤቶች አስተዳደር እነዚህን መብቶች በሚመለከት ከወላጆች ጋር በመመማከር ፖሊሲዎችን በማርቀቅ ላይ ይገኛል እንዲሁም የተማሪዎች የግል ሚስጢራዊ መረጃዎችን የያዙ መጠይቆችና የመረጃ አሰባሰብ፣ግልጽ እንዲሆን ማድረግ ወይም መረጃዎቹ ለገበያ፣ለሽያጭ ወይም ማሰራጨትን በሚመለከት የሚጠበቅበትን በሚመለከት አሰራሮችን በመመልከት ላይ ነው።

የሲያትል ትምህርት ቤቶች አስተዳደር እነዚህን ፖሊሲዎች በሚመለከት ቢያንስ በአመት ውስጥ አንድ ጊዜ ወይም መጠነኛ ለውጥ በሚኖርበት ወቅት በቀጥታ ለወላጆች ያስታውቃል። የሲያትል ትምህርት ቤቶች አስተዳደር እንዲሁ በተወሰኑ ተግባሮች ወይም መጠይቆች የሚሳተፉ ተማሪዎች ወላጆችን ስለሁኔታው እንዲያውቁት ብሎም ልጆቻቸው እንዳይሳተፉ ለማድረግ ያላቸውንም እድል በሚመለከት ለማሳወቅ በፖስታ ወይም በኢሜል በቀጥታ ያስታውቃል። የሲያትል ትምህርት ቤቶች ወላጆች አስተዳደሩ የሚደረገው ተግባራት ወይም መጠይቅ የሚደረግበት ትክክለኛ ወይም ግምታዊ ቀን በዚይን ጊዜ መሆንን ካወቀ ይህንን በትምህርት መጀመሪያ አመት አካባቢ እንዲያውቁት ያደርጋል። የትምህርት አመት ከተጀመረ በኋላ የሚከሰቱ መጠይቆች ወይም ተግባራት ወላጆች ስለ ሚደረጉት ተግባሮች ወይም መጠይቆች ተገቢ በሆነ ሁኔታ እንዲያውቁት ይደረጋል። እንዲሁም ልጆቻቸውን በሚደረጉት ተግባራት ወይም መጠይቆች እንዳይሳተፉ ለማድረግ እድል ይሰጣቸዋል። ወላጆች እንዲሁ የቀረቡትን መጠይቆች አስቀድመይ እንዲመለከቷቸው እድል እንዲሰጣቸው ይደረጋል።

*መብቴ ተጥሶብኛል ብለው የሚያምኑ ወላጆች ከዚህ በታች በተጠቀሰው ጽህፈት ቤት ስሞታቸውን ማሰማት ይችላሉ፤*

Family Policy Compliance Office
U.S. Department of Education
400 Maryland Avenue, SW
Washington, D.C. 20202

ይህ ፎርም ለመረጃ ተብሎ የተዘጋጀ ነው። ይህንን ወደ ልጅዎ ትምህርት ቤት መመለስ የለብዎትም።